
# በእሰመ ሙታን፤



መርዶውን ሰምቼ፤ ሰው ሙቷል መባሉን፤
አላመንኩም ነበር መልዕክት አድራሽውን
ያለ'ስም አርድቶ ግራ ያጋባኝን።

ሞተ ያላችሁት ሙሉጌታን ከሆነ
እሱስ ይኸውና መሃላችን አለ፤
ይኖራል የሞተ እሱን የመሰለ።

ዛሬም ሌላ ሃዘን ሆነና፤ "ሙሉጌታ መንገሻ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ የሚል አዲስ መርዶ ሥሰማ፤ ብቻዬን እርር ኩምትር ብዬ አለቀስኩ። በባዶ ቤትና በባዶ ሜዳ ላይ ማጓጎሩ ቢያስጨንቀኝ፤ አንድ ሁለት የእኔ ቢጤዎችን በስልክ አግኝቼ አስኪበቃኝ ተላቀስኩ። እንዲያ የጨመኩት የሃዘን ዕምባዬ ምንጩ፤ የወንድሜ የጓድ ሙሉጌታና ሌሎች መሰሎቹ ፍላጎትና ዋይታ ወለል ብሎ ሲታየኝ ያደረብኝ የባዶነት ስሜት ነው።

እንዳማረበት ከሸኘነው ከጓድ በላይ (ሳሙኤል ዓለማየሁ) ህልፈት ወዲህ፤ ጊዜያቸውን ሳይሆን ጊዜውን በጠበቀ ክፉ ሞት የተለዩን ብዙዎች መሆናቸው አይዘነጋም። ከነዚህም መካከል እነ ሌንጮን (ሙሉጌታ በትረ)፤ እነ አሥራት አፉን (አሥራት ፋንታዬ ገ/መድህን)፤ ዘገዬን (ዘውዱ መርሻ)፤ አባጋርጠው ኃይሉ ገሞራውን፤ ሩህሩህ ጳውሎስን (ታዬ ጉልላት)፤ መስፍን አርአያ እና ብዙ ተመሳሳዮቻቸውን ያስቧል። እንዳጋጣሚ ሆኖ ብዙዎቹን በቅርብ አውቃቸው ነበር። የሌንጮ ትህትና፤ሕዝባዊ ፍቅርና የትግል ስሜት የሚታወስ ነው። ስሜቱን በግጥሞቹ ከመግለጽ ችሎታው ጋር ያቀራረቡ ስልትና ግለት ወኔ ቀስቃሽ ነበር። ከጳውሎስ የማረሳው ትዝታ አለኝ። ለትግል ጓዱ የሚሰጠው ፍቅርና አክብሮት ከፊቱ ላይ ጎልቶ ይታይበታል። አንዴ ከዋሽንግተን፤ ዲሲ ወደ መኖሪያዬ ስመለስ አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ ሸኘኝና ከመለያየታችን በፊት የማነበው ጋዜጣና መጽሄት፣ የምመገበው ምግብና መጠጥ እየገዛ ያሳቅፈኛል። በቃኝ ብለው አልሰማኝ ብሎ ከምችለው በላይ ያዝኩኝ። ታዲያ ሁሌ ደግነቱና ለጋራው ዓላማችን ያለው እምነት ይታወሰኝ ነበር።ከአሥራት ጋር ከጋራው ጎራ በመለስ በግል ሥራ ጉዳይ በሚኖርበት ኒው ዮርክ አካባቢ ለነበረኝ አንድ ፕሮጀክት ይተባበረኝ ስለነበር በወቅቱ አዘውትረን በስልክና በሌሎች መገናኛዎች እንገናኝ

ነበር። አንዴም ለዚሁ ሥራ ጉዳይ እዚያው ድረስ ሂጄ ተገናኝተን አብረን ረጅም ጊዜ ባሳለፍንበት ወቅት የበለጠ እንዳውቀውና እንዳደንቀው ረድቶኛል። አሥራት ረጋ ያለ፤ ግን ደግሞ ለዛና ፈገግታ የማይለየው አስተዋይና በሳል ወንድም ነበር። ስለ ኃይሉ ገሞራው እዚህ ላይ ቆንስዬ ባላነሳው በተሻለ ነበር። ብዙ ትዝታዎች አሉኝ። በቤተሰቤ ውስጥ ተቀርጾ ከቀረው ትዝታው፤ ብዙውን ጊዜ ወደ እኔ ሲደውል ከውድቅት ሌሊት በኋላ፤ ወይም ሊነጋጋ ሲል ነው። በዚህ ሰዓት ደግሞ ከሀገር ቤት ዘመዶቻችን ሲፈልጉን የሚደውሉበት ሰዓት ነው። እናም ገሞራው ሲደውል ባለቤቴ ብዙዓየሁ የሀገር ቤት ስልክ ነገር ለክፉም ለደጉም ነቅታ የምትጠብቀው ነውና ከተኛችበት ባትታ ተሽቀዳድማ ስልክ ትመልሳለች። ደዋዩ ገሞራው ይሆንና አንዴም አንደበቱ ባረገበ ድምጹ ሰላምታ ይለዋወጣታል። እንደዚህ እያሉ በተደጋጋሚ ሲገናኙ በጣም ተግባቡ። ማስታወሻ ልልክልሽ ነውና ስንት ቁጥር ጫማ ትጫሚያለሽ ብሎ ጥይቅ። በትህትና የተገላገልኩ መስሏት፣ እዉነትም ነው፤ የእግሬ ጫማዎች ትንንሾች ስለሆኑ የሚገጥመኝ በቀላሉ አይገኝምና ስለሃሳብህ አመሰግናለሁ፤ አትስብ ትለዋለች። ታዲያ ገሞራው ይኸን ቀርቀብ ያደርግና፤ ብታንስ ብታንስ ከቻይና ሴቶች አታንስም በሚል መላ ምት፤ ስቶክሆልም ከሚገኝ የቻይና መደብር ሂዶ ለብዙዬ ሁለት ጥንድ ጫማዎች ገዝቶ ላከላት። ሳታስበው ድንገት ደርሷት ለካቻቸውና ልክ ሆነውላት ከውበታቸው ጋር በጣም ወደደቻቸው። ገሞራው የተለየ ፍጥረት ነው አለች። ሞቱን ስትሰማ ከኔ ይልቅ እሷ አምርራ አለቀሰችለት። ዶክተር መስፍን አርአያን ከዝናው ባሻገር፤ ወደ እኛ አካባቢ በእንግድነት ለሕዝባዊ ስብሰባ ጋብዘነው አብረን ውለን አድረናል። እያለፍን ያለውን አስቸጋሪ ዘመን ስንዘከር፤ እንደነ ዶክተር መስፍን አርአያ ያሉ ምሁሮችን ማስታወስ ለመንፈስ ጥንካሬ ዋስትና ይሰጣል። ዶክተር መስፍን ትክክለኛ ምሁርነትን ያንጸባረቀ፤ የተመራመረና ቁሞ የሞገተ ምሁር ነበር። ደስ የሚለው ነገር ብዙው ይለው የነበረው ጉዳይ ሁሉ ደርሶ የጠሉት ሲያፍሩት አይቶ መሞቱ ነው።

ከዘገየ (ዘውዱ) ጋር የምጋራው ረዘምና ሰፋ ያለ ጣፋጭ ታሪክ ነው። በሀገራችን ያ ትውልድ ባካሄደው የትግል ረመጥ ውስጥ እጅ ለእጅ ተያይዘን ወላፈኑን አብረን አልፈናል። ከበዛው ሥንክሳራችን ውስጥ፤ የማረሳለት አንድ ትዝታ አለኝ። ዘገየ (ዘውዱ) በዚያ ቀውጢ የወታደራዊ ደርግ ሥርዓት ዘመን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ውስጥ ገጠር ከሚገኙ ዘመዶቹ ጋር እየኖረ በሙያተኛነት የአንድ አካባቢ የድርጅቱ (ኢሕአፓ) አገናኝ ነበር። ከኔ ጋር አንዳንዴ ቀጥተኛ የሆነ፤ አለዚያም ለተወሰኑ ወራቶች የሚቆይ የጎንዮሽ ግንኙነት ነበረን። አንዱን ቀን ሁለት በአዕምሮና በአካል ጠንካራ የሆኑ አባላት እንታገለው የነበረው ኃይል በክትትል ደርሶባቸው በአስቸኳይ ከአካባቢው እንዲወጡ ይወሰናል። ጓዶቹን በመዋቅር ተቀብዬ በጥንቃቄ እየመራሁ ረዥም የገጠር መንገድ በማቋረጥ ተጉዘን እረፋዱ ላይ ዘገየ ወዳለበት አካባቢ እንደርሳለን። ፊት ለፊታችን ላይ ባለ አንድ የእርሻ ማሳ ላይ እርፍ አጨባበጡና ጅራፍ አያያዙ ደካማ ገበሬነቱን የሚያሳጣው አንድ ሰው በሬዎች ጠምዶ ያርሳል። ጓዶች ከሁዋላ እርቀት እየተከተሉኝ የግድ በዚያው ታከን ማለፍ ነበረብንና ከግንባር ስሄድ እንደነበር ዐይኑ ውስጥ ገባሁና ተያየን። ለይቶኛል፤ እኔም አወቅሁት፤ ዘገየ ነው። አካባቢውን ተመሳስሎ ለመታገል የሚለማመደው ሙያ ነበር። የሚያርስባቸውን የተጠመዱ በሬዎች እንዲቆሙ አደርጎ እርፉን እንደያዘ በአንክሮ ወደ እኔ ይመለከታል። ገስግሽ በመጠጋት ሰላምታ ተለዋውጨው የሆነውንና በአስቸኳይ መደረግ ያለበትን ገለጥኩለት። ፈገግ አለና

“ተበልተሽ አስበላሽን ብዬ እኮ ቆሜ ሚሆነውን እየጠበኩ ነበር” ብሎ አሳቀኝ። በእርግጥም አደጋ ላይ ያለሁና “በጠላት” እጅ ወቄ በመሸነፍ እሱ ወዳለበት መርቼ ያመጣሁ መስሎት ነበር። ወዲያውኑ ወደ ጓዶች አምርቶ ሰላምታ ተለዋወጣቸው። እኔም ግዳጀን መወጣቴን ለጓዱቹ ነግሬ በአስቸኳይ መመለስ ነበረብኝና ወዲያውኑ መንገድ ቀይሬ ወደ ቦታዬ ተመለስኩ። ከዚያም ብዙ ሳይቆይ በአካባቢው ላይና በትግል ህይወታችን ውስጥ ብዙ ነገር ተፈጸመ። የተፈጠረው ሁኔታ ለማንም፤ለምንም አይመችም ነበርና ዘገየ ቦታውን ለቆ ወደ ሠራዊቱ ወይም ወደ ሌላ ቦታ መዛወር እንዳለበት እጠብቅ ነበር። በታእምር ከሞት ተርፌ ሊለመደኝ እምብኝ ያለኝ አዲስ የግል ህይወት ለጥቂት ጊዜ መኖር ስጀምር፤ በአጠቃላይ በድርጅቱ ላይም የደረሰው አደጋ ቀስ እያለ ተገለጠልኝ። እነዚያ የሸኘኋቸው ጓዶችም ከሜዳ ተመልሰው መጠው ኖሮ አገር ውስጥ ተያይተናል። ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ አላውቅም። ከዘገየ ጋር ግን በሰሜን አሜሪካ በሀገርና በግል ጉዳይ አብረን ያሳለፍነው ጊዜ ብዙ ሲሆን፤ ከመሞቱ በፊት ወደ አገር ቤት ተመልሶ መኖር መጀመሩን ተከታትያለሁ። ለምንና እንዴት እንደተመለሰ መጠየቅ ጉዳዬ አለመሆኑን ብረዳም፤ “የአጅሬ” ህይወት በከንቱ እንደማትባክን ግን ይሰማኝ ነበር። ይሁን እንጅ አባ ጅቦ ሞት በውድቅት በሮ ደረሰና ሳይነጋ ወሰደው። ሙሉጌታም እንዲሁ፤ ምንም እንኳ ክቡር ሞቱ፤ “መች ሞቱና ሞቱ ተባለ” ዜማችንን እያደሰና እያጋመረ፤ ስሜት በፈነቀለ ተመስጦ እምባችን እየጠለለ እንድናንጎራጉር የህይወት ተስፋ ቢሰጠንም፤ በአካል ግን ለዘላለሙ ተለይቶን ሙታን ሆኗል። የሚወዱት ልጆቹ፤ እጅግ የሚያፍቅራት ውድ ባለቤቱና መላ ቤተሰቡ ጽናቱን ይስጣቸው፤ ለታጋዩ ማህብረሰብ ክፍልና ለሕዝባችንም ሙሉጌታን በብዙ ሙሉጌታዎች እየተካ ፍትሃዊ ትግሉን እንዲቀጥል የሙታኑ ተጨባጭ ታሪክ የጋራ መደላድል ይሁነው።

በዚህ አጋጣሚ በሃዘን ላይ ሃዘን እየሆነ ከሚከሰትና ከሚያሳዝን ባህሪዎቻችን መካከል፤ የተሰማኝንና የሚከነክነኝን ማካፈል እሻለሁ። ትግል ላይ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ላለመስማማትና ቋሚ የሆነ ህብረት እንዳይፈጠር እርስ በርሱ መታገሉና መሸናነፉ ለደረሰውና እየታየ ላለው ሀገራዊ ትግል መሰናከል እምብርት ነው ብዬ አምኛለሁ። ይህን ዋና ችግራችን ከበው የሚያጅቡትና የሚያባብሉት አያሌ ምክንያቶች ቢኖሩም፤ ቁልፉ ግን ሀገራቸውንና ወገናቸውን ሊታደጉ የሚጥሩ ሁሉ እርስ በርስ መደማመጥ፤ መከባበርና ተባብሮ መምከር አለመቻላቸው ነው። እንደ እኔ ፍርሃት ከሆነ፤ ይህ ድክመት መፍትሄ ካላገኘ ከታሰበው ዲካ ለመድረስ ገና የልጅ ልጅ የሚጓዘው መንገድ እንዳይቀር ያሰጋል። ስህተት ከሆንኩኝ እሰዬው። ከተመክሯችን ተነስተን ሥርዓትን በሥርዓት መቀየሩ በራሱ መፍትሄ እንዳላመጣ መነጋገሩ ለቀባሪው ማርዳት ነው የሚሆነው። ይልቅስ ይህ ከሥርዓት ወደ ሥርዓት የሚሸጋገር አባዜያችን እንዳይቀጥል፤ የማርከሻው መሠረት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መፈተሹና መልስ ማግኘቱ ለነገ የማይባል ቀዳሚ ጉዳይ ይሆናል። በዚህ ዙሪያ ድክመታችን ወሳኝ ሆኖ በብዙ አቅጣጫ ጎድቶናል። ቆመን እንዳንተሳሰብ፤ ሞተን እንዳንቀባበር እንኳ እያደረገን ነው።

የልብ ጓደኞችና ከዚያም በላይ የጋራ ዓላማ አንግበን ለሀገራዊ ትግል ትክሻ ለትክሻ ተደጋግፈን ብዙ ከተጓዝን በኋላ፤ በአሠራርም ይሁን በአመለካከት ልዩነት በመካከላችን አለመግባባቶች ተፈጥረው፤ ወይም

የየግል ባህርያችንና አቅማችን ከዚያ የራቀ መንገድ አብረን መቀጠል አላስቻለን ብሎን ስንለያይ፤ በመጥፎ ስሜት ተሳስበን እንመዳደባለን። ሳይውል ሳያድር ተፈጥሯዊ ግዴታ ነውና፤ ከየበኩላችን የተሰለፉ ታጋዮች ተራበተራ አብረን የሠራነውን የታሪክ አሻራ አንግበው ወደ መቃብር ሲወርዱ እየተመለከትን፤ የምናውቀው በጎ ታሪካቸው አብሮ እንዳይቀበርና ከመሬት በላይ እንዲውል ድምጻችን ማሰማት ይሳነናል። እንደዚህም በማድረግ በአንድ ወቅት አብረን የፈጸምነው የግላችን ታሪክ ከሚቀድሙን ሙታን ታሪክ ጋር ተመሳክሮ እንዲዘገብ የሚያስችለውን ሚዛናዊ መረጃ እንነሳዋለን። ስለሌሎች በጎ ታሪክ ደንታቢስ ስንሆን፤ ከራሳችን ታሪክ ላይ ቀላል ያልሆነ ሚዛን እናንድላለን። ጎራ ለይተን ስለራሳችን ስንተርክ፤ በተግባር ላይ አብረናቸው ሳለን ያዩንንና የሰሙንን ገለልተኛ ምስክሮች ስለማንጠራ፤ ስለራሳችን የምንሰጠው ግምትና እውቅና የተሟላ አይሆንም።

ከየትኛውም ወገን ይሁን፤ ፋና ወጊዎች ይጠቅማል ባሉት ጎራ ላይ ተገኝተው በአባልነትም ይሁን በአጋርነት በቻሉት መንገድና አቅም ለሁላችን መልካም እየተመኙ የበኩላቸውን አስተዋጸኦ አድርገው እሩጫቸውን በሚጨርሱበት ወቅት፤ የሰልፋቸው(ድርጅታቸው) አባልና ደጋፊ ካልሆነው በኩል “የእኛ አይደሉም” የሚል ስሜት ሰፍኖ መታየቱ “ባሏን ጎዳሁ ብላ ...” የሚለውን ራስን በራስ የሚጎዳ ይትበሃል ያስታውሳል። ሙታን ባሰቡት ዓላማና አካሄድ ላንስማማ እንችላለን። ፍላጎታቸው እውን ቢሆን ኖሮ ግን፤ ብዙዎቹ ሕዝባቸውንና ሀገራችውን ቢያኮሩና ቢያስከብሩ እንጅ ለጥቃት አሳልፈው የሚሰጡ ከቶ አልነበሩም። ይህንም እውነታ ለእነ ሙሉጌታ መንገሻ ቁሜ የምመሰክረው ሃቅ ነው። ሠርቶ በሚፈራበት ምድረ አሜሪካ ቤተሰቦቻቸውን ጎድተው፤ በየግል የመበልጸግን ፍላጎትና አቅም ገትተው፤ ደፋ ቀና ያሉት ለሁላችን ብሩህ ተስፋ ሰንቀው ነበር።

ሞት የእያንዳንዳችን ድግስ ነው፤ ስለሆነም ቢያንስ ዳግም ላንገናኝ ስንቀዳደም፤ ጥግ ጥጋችን ይዘን “እከሌ ሞተ”ን ዜና ስንሰማ እዝነ ልቦና ማጣትና፤ አብሶም “የትአባቱ” ማለትን ንቀን የምናውቀውንና ያየነውን የሟች ታሪክ እንመስክር፤ ለእያንዳንዳችን ማንነት ብሎም ለጋራ ታሪካችን መገለጫ ነውና። በሀዘን ለተጎዱ ቤተሰቦችና ለተከታዩ ትውልድ ደግሞ የማይናቅ ብርታት ይሰጣል። ለተሻለ ሥርዓትና ማህበራዊ ኑሮ ለውጥ የሚነሳሳ አዲስ ትውልድ፤ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ሁኔታው አስገግዶትም ይሁን መርጦት በተሰለፈበት ጎራ፤ ‘በስህተቴና በድክመቴ ተጠያቂነቴ እንዳለ ሆኖ፤ለወገኔና ለሀገሬ በታማኝነት የማከናውነው ማንኛውም መልካም ነገር፤ በደከምኩለት ሕዝባችን ዘንድ ያስከብረኛል’ ብሎ ማመን መቻል አለበት እንጅ፤ ‘ከነ እገሌ ጋር ስለሆንክ ወይም ስለነበርክ ሁለመናህ የታሪካችን ጉድፍ ነው’ ከተባለ፤የጋራ ቤትና ታሪክ አይኖረንም። ስለሆነም፤ የጋራ ድርሻ ወይም የጋራ ኃላፊነት ቅኝታችን ካልፈተሽን፤ አሸናፊዎች ከየትም ይምጡ በየት አቋርጠው፤ ሀገሪቱ ሁሉም በየፊናው ያልደከመላት ይመስል፤ ጊዜ ለሰጣቸው አንድ ጎንዮሽ ሲሳይና ታሪክ ሆና ትቀጥላለች። በያለንበት ቅን አስበን በጎ እስከሠራን ድረስ፡ “የእኛው የእናንተም ነው፡ የእናንተውም የእኛ ነው” ብለን መተሳሰብን መልመድ የሚኖርብን ይመስለኛል። ታሪክ የሕዝብ ነው ሲባል፤ ሕዝብ እንደየ ሥምሪቱ በያለበት ጊዜና ቦታ ላይ በግልና በጋራ የፈጠረው ክስተትና ያበረከተው አስተዋጽኦ ድምር እንጅ፤ በአንድ መስፍርትና ዕይታ ውስጥ ተካቶ

ያከናወነው መድበል፤ ወይም ጥቂቶች ባስመዘገቡት ክስተት ተጠቃሎ የሚሰፍር አይይደለም። ስለሆነም የታሪካችን መዝገብ አብላጫው ምዕራፍ በበጎነት ይዘገብ ዘንድ፤እያንዳንዳችን በየአንዳንዳችን ውስጥ የምንኖር መሆኑን፤ ወይም ደግሞ፤ እያንዳንዳችን የየአንዳንዳችን ፍላጣዎች መሆናችን ተረድተን፤ ይሻላል ብለን የተሰለፍንበትን ምድብ ጎራችን እያጠናከርን፤ በአኳያው ደግሞ ለህዝብ ልጆች ከያሉበት በጎ ስሜታችን በመግልጽ፤ሁኔታው ሲፈቅድ ተፈላልገንና እንደማግኔት ተሳስበን ወደ አንድ መድረክ መምጣት የሚያስችለንን ምልክት መሰጣጣት ይኖርብናል። በሞት ሲለዩን ደግሞ የምናውቀውን ሠርተውት ያለፉትን መልካም ነገር 'የእኔ'' ብለን መቀበልና ብስልና ጥሬውን ለይይተን ለትውልድ ማስተላለፍ ነገን የምናስብ ሁሉ ግዴታ ሊሆን ይገባዋል እላለሁ።

ስለዚህም ነው የሙሉጌታና ጓዶቹ ህልፈተ-ሕይወት መሪር ሃዘን፤ በቅርብ ለምናውቃቸውና በትግል ጎዳና አብረናቸው ለተጓዝን ብቻ ሳይሆን፤ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ቅን ለሚያስቡ ሁሉ እንዲሁ መሪር ሃዘን መሆን ያለበት። ሙሉጌታ በትግል ተመክሮ የደነደነ፤ በዓላማውና በራሱ የሚተማመን እውነተኛ ኢትዮጵያዊና ፍትሃዊ ታጋይ ነበር። እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ የሙሉጌታ መንገሻ ልዩ መታወቂያ ባህርይው፤ በመርህ ላይ ጠንቶ መቆምና 'ልክ አይደለም' ብሎ ባሰበበትና በተቃወመው ጉዳይ ላይ ያልተበረዘና ያልተከለሰ - በአድርባይነት ያልተልፈሰፈሰ- ሃሳቡን የመግለጥና የማቅረብ ችሎታው ነው። ይህ ባህርይው ያስቀናኛል፤ ከልቤ አከብረዋለሁ። የእሱ ትውልድ አካል ሆኜ፤ ደግሞም ጊዜ አጋጥሞኝ ከጎኑ ተሰልፌ በመታገል ያየሁትን መመስከር በመቻሌ ሕይወቴን ደስ ይላታል። ሙሉጌታ ቀቢጠ ተስፈኝነትንና እወደድ ባይነትን መጥላቱን፤ የታጋይ ክፍሉን አንድነት፤ መብትና ደህንነት ከሁሉም አስቀድሞ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ያደርገው የነበረው አስተዋጽኦ ትዝ ሲለኝና ምን ያህል በጥረቱ ረክቶ እንደሞተ አለማወቄ ሲታወሰኝ ልቤ በሃዘን ይዝላል። ሙሉጌታ እንደብዙዎቻችን ሁሉ ልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ክስተቶች ሲያሳዝኑትና ሲያስከፉት የነበር ቢሆንም፤ትግላችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ነው ከተባለ፤ "እንዴት እንታገል?" የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ ብቃት የነበረው እሩቅ አሳቢ ታጋይ ነበር። መከባበርና መደማመጥን እንደ ትግል ቆስቋሽነት የሚቆጥረው ሙሉጌታ፤ ለትግል ጓዶቹ ልዩ ክብርና ፍቅር ይሰጥ ነበር። የሙሉጌታ አንጡራ ኢሕአፓዊነቱ የሚነትበው፤ ከትግል ጓደኛው ጀርባ አያሳብቅም፤ ድክመትን መክሰሻና ማነወሪያ አያደርግም። ከአንዳንዶቻችን የደካማነት መንፈስ በሌሎች ላይ ሊንጸባረቅ ቢሞከር፤ሙሉጌታ አብሮ አይነጉድም፤ ይልቅስ የጓዶቹ ጠንካራ ጎንና ያበረከቱት አስተዋጽኦም ግምት ውስጥ ይግባ ይላል እንጅ። ስህተትን በስህተትነት የሚቀበልና መታረም እንዳለበት የሚስማማ ቢሆንም፤ ለአባላት መብትና ድምጽ መከበር ያለማወላወል ግንባሩን የሚሰጥ የዚያ አይበገሬ ትውልድ ጥሩ ምሳሌ ነበር። ምን ይሆናል፤ መሞት የተፈጥሮ ህግ ሆነና በአካል ተለይቶናል።

በድጋሜ ተናፋቂ ልጆቹ፤ ውድ ባለቤቱና ሙሉ ቤተሰቡ ጽናቱን ይስጣችሁ።

**ሙሉቀን ሙጨ**

hawarya.services@gmail.com